Government of Western Australia
North Metropolitan Health Service
Mental Health, Public Health and Dental Services

# ጥርስ ከተነቀለ በኋላ ቀጥሎ መመሪያዎች

## ጥርስ ከተነቀለ በኋላ አስቀጥሎ መከተል ያለብዎት ብዙ የተለያዩ መመሪያዎች አሉ።

## ዛሬ

- መድማትን ለመቆጣጠር እንዲረዳ መሸፈኛ ፋሻ በአፍዎ ውስጥ ይቀመጣል። መሸፈኛውን ከማውጣትዎ በፊት ለ30 ደቂቃዎች ወደታች በደንብ ነክሶ መቆየት።
- ጥርስ ከተነቀለ በኋላ ለ24 ሰዓታት አፍዎን በውሃ አለማለቅለቅ፤ ይህም ለደም መርጋት ሊረብሽ ስለሚችል ነው።.
- አፍዎ ደንዝዞ እያለ መብላት ወይም መጠጣት የለብዎትም። የመደንዘዝ ስሜት ከጠፋ በኋላ በሌላኛው አፍዎ ገጽ መብላትና መጠጣት ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን በጣም ሞቃት ወይም ቀዝቃዛ መሆን የለበትም።
- አፍዎ ደንዝዞ እያለ ከንፈርዎን ወይም ጉንጭዎን እንዳይነክሱት ጥንቃቄ ማድረግ ነው።
- ለደም መርጋት ሊረብሽ ስለሚችል በስትሮው ሰንበሌጥ አድርጎ አለመጠጣት።
- ቀሪውን ቀን እረፍት ማድረግና የአካል እንቅስቃሴን (ስፖርት ወይም የአካል እንቅስቃሴ) ማስወገድ።
- ለ24 ሰዓታት የሚሆን አልኮሆል አለመጠጣት።
- የመዳን ጊዜን ስለሚያዘገይ ለ7 ቀናት የሚሆን ሲጋራ ማጨስን ማስወገድ።

## ነገ

- ግማሽ የሻሂ ማንኪያ በሞቅ ያለ ውሃ ብርጭቆ ውስጥ በማሟት እና ጥርስ በተነቀለበት አካባቢ ቀስ አድርጎ የሟሟውን ውሃ በዙሪያው ማግሞጥመጥና መትፋት።
- ለ7 ቀናት የሚሆን ከምግብ በኋላ እና ከመኘታ በፊት ጥርስ በተነቀለበት አካባቢ ቀስ አድርጎ በጨው ከሟሟ ውሃ ጋር አድርጎ ማጠቡን መቀጠል።

## መድማት

- ለመጀመሪያ ጊዜ ከ12 እስከ 24 ሰዓታት የሚሆን በትንሹ መድማት የተለመደ ነው።
- አነስተኛ የሆነው መድማት ከቀጠለ፤ እጆችዎን መታጠብና ንጹህ የመሸፈኛ ፋሻ ወይም የጥጥ ልብስ በአካባቢው ላይ ማስቀመጥ። ለ30 ደቂቃዎች የሚሆን ፋሻውን በደንብ መንከስ።
- ጭንቅላትዎን ጥቂት ከፍ ቢያደርጉት በጣም ጥሩ ነው።
- መድማቱ ቀጣይ ወይም ከባድ ከሆነ፤ ለእርስዎ ጥርስ ክሊኒክ ያነጋግሩ። ክሊኒኩ ዝድ ከሆነ፤ እባክዎ ምክር ለማግኘት በስልክ 1800 098 818 አድርጎ ከምሽቱ 6:30pm እስከ ጥዋት 8:00am ባለው ጊዜ ይደውሉ።

## ህመም ማስታገሻ

- በቀጣይ 3 ቀናት ውስጥ ህመም ሊያጋጥምዎት ይችል ይሆናል። አስፈላጊ ከሆነ፤ ህመም ማስታገሻ ፓራሲታሞል/paracetamol በመውሰድ በፓከቱ ላይ ያለን መመሪያ መከተል።
- ለበለጠ መድማት ሊያጋልጥ ስለሚችል አስፕሪን/Aspirin ወይም ኢቡፕሮፌን/Ibuprofen (ለምሳሌ ኑሮፌን/Nurofen) አለመውሰድ።
- ስለ ህመም ማስታገሻ መድሃኒቶች ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ለእርስዎ ፋርማሲስት ወይም አጠቃላይ ሀኪም/GP ማነጋገር።

በሚቀጥለው ገጽ ላይ ይቀጥላል

## በቀዶ ጥገና ጥርስ ለወጣ ጎልማሶች በመቀጠል ተጨማሪ መረጃ

- ከቀዶ ጥገና በኋላ እብጠት ሊከሰት እንደሚችል እና ከ36 እስከ 48 ሰዓታት ባለው ጊዜ ከፍተኛ መጠን ሊደርስ ይችላል።
- እብጠቱ መቀነስ የሚጀምረው ከ4 እስከ 5 ቀናት በኋላ ነው።
- እብጠቱን ለመቀነስ እንዲረዳ በእብጠቱ ቦታ ላይ ለ20 ደቂቃዎች የበረድ ፓከት መጠቀም፤ ይህም ከ10 ደቂቃዎች በኋላ በማስወገድ እንደገና መድገም።
- እብጠቱ በሚቀንስበት ጊዜ ትንሽ ጠባሳ ሊፈጠር ይችል ይሆናል።
- Sleep with ከ2 ትራሶች ጋር በመተኛት ጭንቅላትዎ በመጠኑ ከፍ ሊል ይችላል።
- አፍዎን ለመክፈት ችግር ሊሆንብዎት ይችላል ይሆናል። ይህ የተለመደ እንደሆነ እና እብጠቱ እየቀነሰ ሲሄድ አፍዎን ለመክፈት ቀለል ይላል።
- አስፈላጊ ከሆነ አመጋገብዎ በፈሳሽና ለስለስ ባለ ምግብ ብቻ ማድረግ። በቀጣይ ሳምንት ላይ ቀስ በቀስ እያደረጉ ወደ መደበኛ አመጋገብዎ መመለስ።
- በተቻለ መጠን ወደ መደበኛ ጥርስ መቦረሽን መጀመር።
- ቀጣይ የሆነ የመደንዘዝ ችግር ካጋጠመዎት፤ እባክዎ ከዚህ በታች ባለው ክሊኒክ ቁጥር ያነጋግሩ።

CLINIC
STAMP

## ለበለጠ መረጃ እባክዎን ከእርስዎ ጥርስ ባለሙያ ጋር መነጋገር

### የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ውቀውይም አስተያየት መስጠት ከፈለጉ?

ይህ ሰነድ በሌላ አማራጭ የተለያየ ቅርጽ ሊቀርብ ይችላል፤ ይህም በጥያቄ በ braille, audio tape ወይም electronically ይሆናል.

Communications Officer, Dental Health Services
Locked Bag 15, Bentley Delivery Centre, WA 6983

(08) 9313 0555

publications@dental.health.wa.gov.au

www.dental.wa.gov.au

በዚህ ሰነድ የተጠቀሙት ማንኛውም ቅርጽ/ስእል ለመግለጫ ተብሎ ብቻ እንደሆነ ይህም ለአጠቃላይ መመሪያ ለማቅረብ ብቻ ነው።

CONSUMER REVIEWED

HealthyWA Health information for Western Australians

© 2020 Dental Health Services WA. All rights reserved.

DHS14 v 09/22_Amharic